# ለምን ይዋሻል? እስከመቼስ ይዋሻል?

## ክፍል 5

*ኢትዮጵያን ማን በደለ? ማን ለጦርነትና አደጋ አጋለጣት? ማን ለድህነት ዳርጎ የረሀብ ምሳሌ አደረጋት? ማን አዳከማት? እነማን ለግንጠላ ዳረጓት? ለባዕዳን አጋልጠው ሰጧትና ሉዓላዊነቷን አስደፈሩ? ማን ህዘቦቿን ፈጀ? ጨቆነ? ለግፍ ዳረገ ?*

*መሰረታዊና ዋና ዋና ጥያቄዎች ሲቀርቡ ለዘመናት ሲደለቅ የቆየው የሀሰትና የውሸት ከበሮ ይበሳሳል፤ አድማጭም ያጣል። ገኖና ከነጎደጓድ በላይ ጆሮን ስማ እያለ የሚጮኸው ሀቅ ለኢትዮጵያ መከራና ዛሬም ላለችበት አደገኛና አሳሳቢ ሁኔታ ተጠያቂ ኢሕአፓና ታግሎ የተሰዋው ጀግና ትውልድ ሳይሆኑ አገዛዞቹና ስርዓቶቹ መሆናቸውን ግልፅ ጥርት አድርጎ ያሳያል፤። ወደ አፄው ስርዓት እይታችንን ስንመልስ፤*

- 85 *በመቶውን ዜጋ ገባርና ጪሰኛ አድርጎ የበደለውና የጨቆነው ይህ አገዛዝ ነው።*
- *ምልዓተ ህዝቡን መሰረታዊ መብት ነፍጎ በባርነት ደረጃ የገዛው ይህ ስርዓት ነው።*
- *መሰረታዊ ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን ያፈነውና ሕዝብን ለአመፅ የገፋፋው ይህ አገዛዝ ነው።*
- *በብሄረሰብና ሀይማኖት ደረጃ እኩልነትን ሰርዞ ልዩነትና በደልን ያሰፈነው ይህ ስርዓት ነው።*
- *ኢትዮጵያን ለአሜሪካ አሳልፎ ሰጥቶ ሉዓላዊነቷን ያስደፈረው ይህ አገዛዝ ነው።*
- *የኤርትራን የፌዴሬሽን ትስስር አፍርሶ ለልዩነት ሀይሎች የጠቀመውና ቀጣዩን የኤርትራ ችግር የቀፈቀፈው ይኸው አገዛዝ ነው።*

*ኢትዮጵያ ለጥቂቶቹ ገነት ለብዘሁኑ ደግሞ ገሀነምና እስር ቤት ነበረች። የአፄውን ዘመን ዛሬ በዘፈንና በቃል የሚያሞግሱ የታሪክ አላዋቂዎችን ወደ ጎን ስንተው ሀቁ ግን ያ አገዛዝ የፈላጭ ቆራጭና ጨቋኝ አገዛዝ ጊዜ መሆኑን ያሳየናል። ዛሬ ይህን በመካድ የፈረደበትን ዋለልኝ ሀገሪቷ ለብዙሃኑ እስር ቤት ናት ብሎ ያበጠውን በማፈንዳቱና ሀቁን በመናገሩ የሚያወግዙ ሁሉ መጠጣት ያለባቸው እሬት ነው። መልዕክቱ ሀቅ ሆኖ ሲመጣ መልዕከተኛውን መግደል መፍትሄ ሆኖ አያውቅም፤ ዛሬም አይሆንም። ያ ትውልድም የነበረውን ሁኔታ አጢኖ የመሰለውንም ምላሽና መፍትሄ በመስጠት የሀገሩን አንድነት ለማረጋገጥ ጣረ እንጂ ችግሮቹን ሁሉ የፈጠረው የነበረው ስርዓቱ ነበር። ያኔ ጭቆና አልነበረም ብለው የሚክዱ ሁሉ ከሀቅ የተጣሉ ናቸው። የጭቆናውን ሁኔታ በዴሞክራሲና እኩልነት መንገድ ለመፍታት ጥረቱ ሲጀመር ጠባቦች ደግሞ በበኩላቸው የአማራውን ሕዝብ ሁሉ በገዢ መደብ ደረጃ ፈርጀው፤ ከጭቆናው ተጠቃሚ አድርገው ወዘተ ሊሰብኩ ሲጀምሩ ገና ከዚያው ጊዜ የታገላቸውና የተቃወማቸው ኢሕአፓና ያ ትውልድ መሆናቸው ከቶም ሊካድ አይችልም። ዛሬ ጊዜ አለፈ ብለው እነ ዋለልኝንም ሆ ያን ትውልድና*

ኢሕአፓን በሀሰት ሊወነጅሉ የተነሱት ክፍሎች ያኔ የት ነበራችሁ፤ ምን አደረጋችሁ፤ ምላሳችሁን ድመት ቆረጠው በላው፤ ብዕራችሁ ቀለም አጣ ተብለው ቢጠየቁ መልሳቸው ወይም ውሸት ወይም ዝምታ መሆኑ ደግሞ የሚታወቅ ነው:: ያ ትወልድ የነበረውን ጭቆና አምኖ በዴሞክራሲ መፍትሄና በመብት እውቅና ጎዳና አንድነትን ሲፈልግ ጠባቦች በዕንፍ ለግንጠላ መጓዛቸው ትውልዱን ተጠያቂ አያደርገውም:: በሀገረቷ ዴሞክራሲና ፍትህ ሰፍኖ በነበር ሁሉም ችግሮች መፍትሄ አግኝተው ሀገር በቀና ጎዳና ተጉዛ በተገኘች ነበር:: ብዙሀኑን ለብዝበዛ ዳርጎና መብት አልባ አድርጎ አፀያፊ ስርዓትን ያሰፈነው የአፄው አገዛዝ ለተከተለው ችግር ሁሉ ተጠያቂ ነበር/ነውም::ባዕዳን የሀገር ጠላቶችም ይህን የተገኘ ዕድል ተጠቀሙበት እንጂ ራሳቸው በራሳቸው ችግሮቹን አልወለዱም:: የጭቆና ስርዓት አመፅን ይወልዳልና የካቲት አብዮትን አርግዞ የወለደው ራሱ የአፄው ስርዓት ነው::

የአገዛዙን ስህተቶችና ድክመቶች ለማረምና ለማስተካከልም ብዙ ጥረቶች ነበሩ:: እነ በላይ ዘለቀ ተሰቀሉ፤ እነ ደጃዝማች ታከለ ወልደ ሐዋርያት ተሰዉ :: ከመንግስቱ ንዋይ በፊትና ከዚያም በኋላ የተሞከሩ መፈንቅሎች ከሽፈው የሞከሩት ተገደሉ:: ብዙዎቹም ታሰሩ፤ ተጋዙ:: ስርዓቱ ለጥገና ለውጥም ቢሆን እምቢ አለ :: የነበረው አማራጭ አመፅ ብቻ ነበር:: በባሌ፤ በጎጃም፤ ያኔ ደራሳ ይባል በነበረውም ወዘተ አርሶ አደሮች አመፁ:: ሁሉም በአገዛዙ ወታደሮች ተጠቁ:: በአርሶ አደሮቹ ላይ ግፍ ተፈፀመ :: በወቅቱ ያለውን የአገዛዝ ቀውስና ችግር ተረድቶ ስርዓቱን ለማዳን የሚጥር ከበርቴ ክፍል አልነበረም:: ግትሩ ስርዓት አብዮትን በራሱ ላይ ጋበዘ :: የሕዝብን የልብ ትርታ ለማዳመጥ ደግሞ ዕብሪቱ አልፈቀደለትም-- ሕዝብን ይንቅ ነበርና:: አፄው የመለኮት ምርጥ ነኝ ባይ ነበሩና:: መኳንንቱና ከበርቴዎቹም ምርጦች ነን ማን ሊነካን ባዮች ነበሩና :: በወቅቱ ምርጦቹ ሲጠየቁ የሀገሩቷ ሕዝብ ቁጥር ከ እኛ ውጪ ከ500 አይበልጥም አሉ የተባለው የነበረውን ሁኔታ አጋኖም ቢሆን ይገልጠዋል:: በገዢዎችና በብዙሀኑ ተገዢ መሀል የነበረው ልዩነት በጣም ሰፊና በሰላምና ዕርቅም የሚጠብ አልነበረም:: ስለሆነም የጥገና ለውጥ ይደረግ ዘንድ ለንጉሱ አፄ ሆይ እያለ አቤቱታ ያቀርብ የነበረው ተማሪና ወጣት ሁኔታውን ተረድቶ ወደ ስር ነቀል ለውጥ አማራጭ ኮበለለ :: አፄው በ1953 እነ ገርማሜና መንግስቱ ንዋይን ከሰቀሉ በኋላ ራሳቸው ከጥገና ለውጡ ጋር ተቆራረጡ ማለት ይቻላል:: የሕዝብ ጥያቄ የሆነውመሬት ለአራሹም ሲስተጋባ ለጩኸቱ ጆሮአቸው መደፈኑም ችግሩን አባባሰው:: የተማሪውን እንቅስቃሴ በአፈና ለማስቆም የተደረገው. ጥረትና ጥላሁን ግዛውንም ለመግደል የተወሰደው እርምጃ የተበላሸውን ሁኔታ ይበልጥ አጋገመው:: ችግሮችን ለመፍታት ሆነ ቅራኔዎችን ለማርገብ ምንም እርምጃ አልተወሰደም:: አገዛዙ ታውሮ እየተባለሸ የነበረውን ሁኔታም ሊረዳም ሆነ ሊገነዘብ የሚችል እነበረም:: በመሆኑም የካቲት 66 ን ወለደ-- የራሱን ጥፋት::

ምርጥ መኮንኖችም በየካቲተ 66 የሕዝብን አብዮት ማጅራት ሲመቱ የመጀመሪያውን ስህተት ፈፀሙ። ለስር ነቀልና ዴሞክራሲያዊ ለውጥ በመስዋዕትነት ተከፍቶ የነበረውን በር ክርችም አድርገው ዘሎት--ቀረቀሩት። ለውጥ አለምንም ደም ብለው ሊያወናብዱ ቢሞክሩም በጉልበታ ውየሕዝብን ድል ቀምተዋልና ደም ሳያፈሱ በስልጣን የሚቀጥሉበት ሁኔታ ከቶም አልነበረም። ሳይውሉ ሳያድሩ ወደ አፈናው ተረማመዱ። አፍኑ ምቱ፤ ለሲቪሉ ስልጣን እንዳትለቁ፤ ጠመንጃ ውን ይዛችሁ ምን ትጠብቅላችሁ ብለው መካሪ ዶክተሮች ዛሬ ተቃዋሚ ድርጅቶችን መሪዎች ነን ማለታቸውን ሳንጠቅሰው አናልፍም። ደርግን በፀረ ሕዝቡ ምርጫው ያበረታቱት ለተከተለው ቀውስ ሁሉ ከደርግ እኩል ተጠያቂ ናቸው። ኢሕአፓ የተያዙትን ሁሉ የአፄው ስርዓት ባለሰልጣ ኖች ረሸናቸው ብሎ መስመርም አልፃፈም፤ ጥሪም አላደረገም። መርማሪ ኮሚሽን አባል የሆኑና ምን ትጠብቃለህ በላቸው ያሉ ሌሎች ናቸው። ወደ ሐራሬ የኮበለለው አረመኔ ማንነታቸውን ራሱም አጋልጧል። የአብዮቱን ድል ደሙን ያፈሰሰው ሕዝብ ተጠቃሚ እንዲሆን በሚልም ኢሕአፓ ሁሉን አቀፍ ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግስት ይቋቋም የሚለውን መፈክር ቢያቀርብም ደርጉና ደጋፊዎቹ ለዚህ ጥሪ የሰጡት መልስ ኢሕአፓም ለማጥፋት መጣር ነው። ኢሕአፓ ከደርጉ ደጋፊዎች ቡድኖችም ጋር ግጭትን መፈለግ ሳይሆን ከተቻለ በሚል መግባባትን በመፈለ ግ በተደጋጋሚ ተወያይቶ ልዩነቱ ግን ወሳኝና መሰረታዊ በመሆኑ ለመግባባት አልተቻለም። ኢሕአፓ ያኔ ይባል እንደነበረው ጠመንጃ ለማንሳት አልተሯሯጠም፤ የፈለገው መንገድ ሰላማዊ ግን ዴሞክራሲያዊ ነበርና አምባገነንነትን የመረጡት ጋር ሊስማማ አልቻለም። በየካቲት አብዮት ለኢትዮጵያ አዲስ ምዕራፍ ተከፍቶ ነበር፤ የነበሩ ችግሮችንም--የኤርትራውንም ጨምሮ-- በሰላ ማዊና ዴሞክራሲያዊ መንገድ መፍታት ይቻል ነበር። ይህ እንዳይሆን ግን ሻለቃ መንግስቱና መሰሎቹ እንቅፋት ሆኑ። የስልጣን ጥማቸው መረን የለቀቀ ነበርና የሀገርና የሕዝብን ፍላጎት ከቁም ነገር አላሰገቡም። በአዋጅና አፈና መብቶችን አደባዩ። ሳይውል ሳያደርም በኢሕአፓ ና በሕዝብ ላይ ጦርነት አወጁ። እነ ጄኔራል አማን አንዶምና ሌሎችንም በህገ ወጥ መንገድ ከገደሉ በኋላ በኤርትራ አሰቃቂ ግድያዎችን በኮማንዶዎቻቸው መሳሪያነት በተለይ በወጣቶች ላይ በማካ ሄድ የኤርትራ ወጣቶች ወደ ግንባሮቹ እንዲሸሹ አደረጉ። ወደዱም ጠሉም ግንባሮቹን አጠናከሩ ። ይህ ድርጊታቸው ተደጋግሟል። አረመኔው ኮለኔል ብዙ መኮንኖችን በኤርትራ እየረሸነ የጦሩ ን ሞራል በመስበር ለግንባሮቹ ረድቷል። በኦጋዴን ጦርነት ጊዜም ስንቶቹም መኮንኖችና ወታደሮች ኢሕአፓዎች ብሎ በመረሸን እንደፈጀ የሚታወቅ ነው። የሀገር አንድነት ጥረቶችን ሠያከሸፈው አገዛዙ ራሱ ነው።

ማን ችግሮችን አባባሰ? ማን ሕዝብን ከፋፈለ? ማን የሀገርን መካላከያ አዳከመ? ለሚሉት ጥያቄ ዎች መልሱ ደርጉ ራሱ የሚል ነው። ደርጉም ተመቶ በግለሰብ የበላይነት የተተካ ነበርና ለጥፋቱ ሁሉ ተጠያቂ ዛሬ ወደ ዚምባብዌ የፈረጠጠውና የዚሁ አረመኔ ጀሌዎች መሆናቸውን መደበቅ

አይቻልም:: የሶማሊያ ወራሪ ጦርም ለድል የበቃው ደርጉ ሕዝብን አስቀይሞና ከፋፍሎ በመገኘ ቱ እንጂ ኢሕአፓ ወራሪውን ደግፉ ብሎ በመቀስቀሱ አይደለም:: ይህን ውሸት ዛሬም የሚደጋግ ሙ ቢኖርም ሀሰት መሆኑ ግልፅ ነው:: ጦሩና ሕዝቡ ደርግን ደግፏል እየተባለ ባለበት ሰሚና አድማጭ የለውም ይባል የነበረው ኢሕአፓ እንዴት ነው የመላ ጦሩን ጆሮ አግኝቶ ሊያኮላሸው የቻለው? ሀቁ ግን ኢሕአፓ የሶማሊያን ወረራ መቃወሙንና አባሎቹም ሲታገሉ መሰዋታቸው ን ያረጋግጣል:: ሀቁ ኢሕአፓ በሰላማዊ ፖለቲካዊ ትግል ተሰማርቶ ሳለ ደርግና አጋሮቹ በኢሕአ ፓ ላይ ጦርነት ማወጃቸውንና ፍጅት ማካሄዳቸውን ይመዘግባል:: አሊ ሙሳ፣ ጌታቸው ሺቢሺና ሌሎችም ያካሄዱተትን ግድያ ይጠቅሷል:: የህገ ወጥ አገዛዝ ኢፍትሃዊ እርምጃዎችን ለመቃወም የፈነዳውን አብዮት ያጨናገፈው ደርግ 60 የቀድሞ ባለስልጣኖችንና ህግ ወጥነቱን የተቃወሙ መኮንኖችን አለፍርድና ፍትህ በመረሸኑ ፀረ ፍትህ የሆነ የወሮበሎችን አገዛዝ ሊያሰፍን ቻለ :: የተያዙ አለምንም ፍትህና ፍርድ የሚረሸኑበት:: ነፃ እርምጃና አብዮታዊ እርምጃ በሚል ብዙ ሺ ዜጎች በገፍና በግፍ ተገደሉ:: ለአዲስ ስርዓት ሕዝብ የነበረው ምኞትና ፍላጎት አፈር በላ:: ህገ ወጥነት ሰፈነ :: በዚህም የተነሳ ኢሕአፓና ሕዝብ ያቀረቡት ተቃውሞ ሰላማዊ ቢሆንም በክብ ረ ነክ ተፈርጆ ለአፈና ተዳረገ :: የኮለኔል መንግስቱ ጭራቅ አገዛዝ በሁሉም መስክ የሕዝብን ሰቆ ቃ አባባሰ:: ዝርዝሩን ሕዝብ የሚያውቀው ነው::

ኢሕአፓ በዚህ ወቅት ይህን ወታደራዊና ማንም ያልጠራው አጉል ሞግዚት አገዛዝ ተቃውሟል:: ሕዝብ ለምን እንደታገለና ምን ውጤት እንደሚፈልግም ግልፅ ነውና ሁሉን አቀፍ ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግስት ይመሰረት፣ ችግሮች በሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ ውይይት ይፈቱ፣ የሀገር ሉዓላ ዊነት ይከበር ብሎም ታግሏል፣ ሕዝብንም አነሳስቶ ለዴሞክራሲ ተዋድቋል:: ይህን ጥፋት የሚሉ ካሉ ኢሕአፓ ጆሮ አይሰጣቸውም:: ለጨቋኝ አገዛዝ ባርነትን ኢሕአፓ በማንኛውም ማጠየቂያ ተለውሶና ተቀባብቶ ቢቀርብ መቼም ቢሆን መቼ የሚቀበል አለመሆኑን የ38 ዓመት ተመክሮው ግልፅ ያደረገው ሀቅ ነው:: የከሀዲና አድርባይ ከበሮ በኢሕአፓ ተደምጦም አያውቀምና:: የኢትዮጵያን ቀውስ ያባበሰውና ያን ሁሉ ችግረ የፈጠረውም ደርግ እንጂ ሌላ ማንም አልነበረም :: የሕዝብን አብዮት በማጨናገፉ:: የሕዝብን መብት አፍኖ አመፅን በመገፋፋቱ:: ሕዝብን በፍጅ ት በመጨረሱና በመበታተኑ:: ዛሬ ወያኔ በኢትዮጵያ ላይ ሊጨፍር የቻለው ዕድሜ ለደርግ እያለ መሆኑን በመካድ የዚያ አገዛዝ ቁንጮዎችን በጀግንነት ፈርጀው ሊያሞግሱ የተነሱ ከሀዲዎች ቢኖሩም ሀቁ የሚያረጋግጠው ግን ኢትዮጵያን ያዳከመ ÷ ያደማ፣ የበታታነና ለወያኔ አጋልጦ የሰጠ የኮለኔል መንግስቱና ኢሠፓ አገዛዝ መሆኑን ነው:: ለመዘርዘር፣

- ማነው የየካቲት አብዮትን ያደናቀፈና ሕዝብን ስልጣን የቀማ?
- ማነው ዴሞክራሲያው መብቶችን በአዋጅ የከለከለ?
- ማነው በራሱ በደርግ ውስጥ የተከሰቱ የለውጥ እንቅስቃሴዎችን በግድያ ያፈነ?
- ማነው ህገ ወጥነትን አንግሶ አለፍርድ እስረኞችን የረሸነ?
- ማነው የኤርትራን ችግር በአግባቡ ይዞ በመፍታት ፈንታ ፍጅትን መርጦ ለግንባሮቹ ስንት ሺ ጀሌዎችን ያበረከተ?

- ማነው የብሄረሰብን ጉዳይ ለፖለቲካ ጥቅሙ በማዋልና ተቃዋሚዎችን በአማራነት ፈርጆ ሌሎችን በግድያና ሽብር ያሰማራ?
- ማነው ራሱን በአፈና ያጫጫና ስልጣንን ለአንድ ግብዝ ፈሪና ጨፍጫፊ ግለሰብ ያስረከበ?
- ማነው የኮታን ስርዓትና አንጉለ ሰፈራን በአርሶ አደሩ ላይ ጥሎ ረሀብን ያመጣ?
- ማነው የራሱን አዋጊ መኮንኖች በሰበብ አስባቡ የጨፈጨፈና ጦሩን ያዳከመ ?
- ማነው የሀገራዊ ዕርቅ መንገድ ሲፈለግ ፈላጊዎችን ያረደ?
- ማነው አጋር ያላቸውን ቡድኖች አንድ ባንድ ያፈነ?
- ማነው ሀገሪቷን ለሶቭየት ህብረት የሸጠ ?
- ማነው አንድን ውዳቂ ግለሰብ በጣዖት ደረጃ ሊያሰቀብል ደፋ ቀና ሲል ጊዜና ህይወት ያጠፋ?
- ማነው የራሱን ጦር የከፋፈለና ያዳከመ?
- ማነው ሀገርን አጋልጦ ጥሎ የፈረጠጠ ?

ወዘተ ወዘተ ብዙ ጥያቄዎች ቢደረደሩ መልሱ ደርግ ወይም የኮለኔል መንግስቱ አገዛዝ የሚል ነው፡፡ ሌላ የሀቅ ምላሽ የለም/ሊኖርም አይችልም፡፡ ይህ አረመኔ አገዛዝም ቢሆን የመታረሚያና መስተካካያ መንገዶች በየጊዜው ተጠቁመውለት ነበር፡፡ ሊገለብጡት ከሞከሩትም እንኳን ሊማር ይገባው ነበር፡፡ አረመኔው ኮለኔል ግን መካሪዎቹን ሁሉ አርዷል ወይም አግልሏል፡፡ ሊወገድ አካባ ቢም በጣሊያንን ፈረንሳይ መንግሰታት አማካኝ.ነተ የቀረበለትን የሽግግር መንግሰት አማራጭ እምቢኝ ብሎ ክተት በማወጅና ህዝብ መብት አለህ ቢባል የመጀመሪያ ሰልፉ መንግሰቱ ይሰቀል የሚል ይሆናል ብሎ በማሾፍም ሁኔታዎችን ለወያኔ አመቻችቷል፡፡ የሀገር ህልውናም ለእሱ ዋና ጉዳይ ባለመሆኑ ስልጣኑንና የበቀል ስሜቱን ለማሟላት ሲል አዛውንት ጄኔራሎችን አንቆና ረሽኖ የጦሩን ሞራል አድቅቋል፡፡ በሰሜን ግንባርም የራሱ ሆዳም ጄኔራሎች ጠላት ለተባለወ ቡድን ምስጢር እያጋለጡ ስንቱን ወታደር አስፈጅተዋል፥ ለሽንፈትም በር ከፍተዋል፡፡ ዛሬ በርካታ ወንጀለኞችና ከሀዲዎች በስደት ዓለም በተለይ በአሜሪካ ታሪካቸውን ደብቀው መኖራቸ ው ደግሞ የሚታወቅ ነው፡፡ ወደ መጨረሻውም የአገዛዙ ቁንጮዎች ራሳቸው ለአሜሪካ ቅጥረኛ ሆነው አንድም ህዝብን በመሸጥና ወደ ባዕድ በማጓጓዝ በሌላም በኩል ደግሞ የሀገርን ወሳኝ ምስጢሮች አሳልፎ በመስጠት ለወያኔና ሻዕቢያ ድል ከፍተኛ አስተዋፅዖ አድርገዋል፡፡ ለሀገር ብለው ያገለገሉ ስንቶቹ ሰማቸው ተጋልጦ ለጠባቦቹ በከሃዲነት ሰለባ ሆነዋል፡፡አምባገነኑም ፈሪና ወራዳ ነውና ውጣ ሲባል ላጥ ብሎ የሀገር ገንዘብ ዘርፎ ወደ ሙጋቤ ሀገር መፈርጠጡ የታየ ነው፡ ፡ ማንነቱ የአርበኞች ሳይሆን የባንዳዎችና ፈርጣጮች መሆኑንም አረጋግጧል፡፡ ዛሬ ታዲያ ትዝታዬ እያለ ሲመፃደቅና ይህንንም ውሸቱን ብዙዎች ገንዘብ ከፍለው ገዝተው ሲያነቡ መታዘ ብ መገደዳችን መቸም ያሳዝናል፡፡

ወያኔና መሰሎቹ ደርግን ታግለን ድል አደረግን የሚሉት የመመፃደቂያ ልፈፋ ውሸት መሆኑን ደርግን ታግሎ ያዳከመውና ለውደቀቱም ከፍተኛ አስተዋፅዖ ያደረገው ሕዝብ ሁሉ ያውቃል:: የሻዕቢያና ወያኔ ሁሉን አድራጊና ድልን ፈልቃቂ ልፈፋ መሰረተ ቢስ ነው:: ደርግን ገዝግዞ የጣለ ው ደሙን ያፈሰሰው የኢትዮጵያ ሕዝብ ነውና:: ዛሬ በጠባብነት ያዙን ልቀቁን የሚሉ ቡድኖች ም ያኔ የደርጉ ቀኝ እጅ ሆነው የቀይ ሽብሩም አራማጅ መሆናቸውን የምንረሳው አይደለም:: ኢሕአፓን በአማራ ድርጅትነት ፈርጀውና ደርጉ የጭቁኖች መንግስት ነው ብለው በቀበሌና ከፍተኛ ታጣቂነት ስንቱን የኢሕአፓ አባል የፈጁት ዛሬ የተቃዋሚ ድርጅት አባል ነን ብለው ሲሸፋፈኑም ሀቁን አናነሳም ብለን ዝምታን እንድንመርጥ መጠበቅ የለበትም:: ወያኔንም ዴሞክራ ሲያዊ መንግስት ብለው ያቀፉትም መሆናቸውንም ማንሳት የግድ ይሆናል:: እነዚህ ዛሬ ተገልብ ጠው በኢሕአፓ ላይ ውሸትን ቢያሰራጩ የሚገርመን አይሆንም:: የኢሕአፓ ጠላቶች የኢትዮጵ ያ ጠላቶች ናቸው:: ኢሕአፓን የሚጠሉት ለኢትዮጵያ የቆመና በኢትዮጵያ ጥቅም ላይ ከቶምና መቼም የሚደራደር አይደለም በሚል ነው:: ሞክረውት አልሆነላቸውም:: ሱዳን፤ ሶማሊያ፤ አሜሪካ፤ አረቦች ሁሉም ሞክረውታል:: አሜሪካ ከአንዴም ሁለት ሶስቴ ኢሕአፓን ለማጥፋት ጥራለች:: ሰላዮቿን አሰርጋ ለማግባት ሞክራ ከሽፎባታል:: በሌሎች ድርጅቶች አማካኝነትና በሱዳን ተባባሪነት ወረራ አካሂዳም ለማጥፋት ያደረገችውንም ሙከራ ኢሕአፓ/ሠ አይመቱ ም ት መትቶ አክሽፎታል:: በአሜሪካና ጀርመን ቁጥጥር ስር ያሉት ራዲዮኖችም ቢሆኑ ለዓመታት ኢሕአፓን የሚያገልና ደጋፊ የሚያሳጣ ፕሮፓጋንዳ ሲያካሂዱ የቆዩ ሲሆኑም ዛሬም በዚሁ ተልዕ ኮአቸው ተሰማርተው አሉ:: ሕዝብ የታዘበውና እየታዘበም ያለው ነው:: ጠባቦች በጋራም ሆነ በተናጠል ኢሕአፓ ላይ ያካሄዱትና እያካሄዱ ያሉትም ዘመቻ የሚታወቅ ነው:: አንጃና በታኙን አይዞህ ብለዋል፤ መድረክ እየሰጡም ሊያሰወድዱ ሞክረዋል:: ልዩ ልዩ ኢሕአፓን ያገለሉ የግንባ ር ምስረታ ጥረቶች ተሞክረወም ከሽፈዋል፤ ዛሬም እየተሞከሩ ናቸው:: ይህ ሁሉ ደፋ ቀና በተለ ይም ህልውና የለውም በሚባል ድርጅት ላይ የሚካሄደው አለምክንያት አይደለም:: ኢሕአፓ ከተመሰረተ ጀምሮ ለኢትዮጵያ ሕዝብና ሀገራዊ ጥቅም የቆመና ይህንንም አሳልፎ የማይደራደር ዛሬም በትግል ላይ ያለ ኢትዮጵያዊ ድርጅት በመሆኑ ነው:: ስለዚህም ፀረ ኢትዮጵያ የሆኑት ባዕዳን ሆኑ ሀገር በቀል ከሀዲዎች ውድቀቱንና መጥፋቱን ይመኛሉ:: የውሸቱና ክሱ ጋጋታ ከዚህ የተነሳም ነው:: ለምን ይዋሻል ስንል መልሱ ውሸት ለኢሕአፓና ለኢትዮጵያ ጠላቶች ዋና መሳሪ ያና አስፈላጊም በመሆኑ ነው የሚል መለስ ይሰጣል:: እሰከመቼ ስንል ደግሞ የኢትዮጵያ ጠላቶ ች በሞላ ድባቅ እስኪመቱ የሚለው ነው ምላሹ::

ኢትዮጵያን ማን በደለ? ማን ለጦርነትና አደጋ አጋለጣት? ማን ለድህነት ዳርጎ የረሀብ ምሳሌ አደረጋት? ማን አዳከማት? እነማን ለግንጠላ ዳረጓት? ለባዕዳን አጋልጠው ሰጧትና ሉዓላዊነቷን አስደፈሩ? ማን ህዘቦቿን ፈጀ? ጨቆነ? ለግፍ ዳረገ ? መልሱ ግልፅ ነው-- ወንጀለኞቹ በሕዝብ ላይ ተጭነው የነበሩና ያሉ አረመኔ ስርዓቶች ናቸው:: በተለይም የዛሬው ወያኔ!

ይቀጥላል